# Claiming This Flag!

## *ይህ ሠንደቅ ዓላማ !*

**ፀሀፊ፤ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ**
**ትርጉም፤ መስፍን ማሞ ተሰማ**

***********************************************************

*__ማስታወሻ፤__* **"Claiming This Flag!"** *የሚለውን የእንግሊዝኛ ፅሁፍ ያነበብኩ ጊዜ የፅሁፉ ዓላማ ጥልቀትና የመልዕክቱ ግዝፈት ከወቅቱ የሀገራችን ህዝባዊ ተጋድሎ ጋር ተዛምዶ የተነባቢነቱ አድማስ ይሰፋ ዘንድ ተመኘሁ። ሀገራችን ኢትዮጵያ በምትገኝበት በዚህ ፈታኝ ወቅት አእላፍ የኢትዮጵያ ትንታግ ወጣት ትውልድ የጥንት የመሰረቱን ሠንደቅ ዓላማ ከሰሜን ከደቡብ፤ ከምሥራቅ ከምዕራብ ከፍ አድርጎ በማውለብለብ* ***ከሀገር በቀሉ ዘረኛ ቅኝ ገዢ ህወሃት እና የንፁሀንን ደም በማፍሰስ ከሰየጠነው አንጋቹ ኢጋዚ ጦር ጋር ስለነፃነቱ እየተፋለመ ሲወድቅ*** *እንዲህ ያሉ ፅሁፎች ለትግሉ ገንቢ ለፅናቱም ምርኩዝ ለሞራሉም ምሶሶ ናቸው። እንዲህም በመሆኑ በራስ አነሳሽነት ትርጉሙን ስሰራ ፀሀፊውን አማክሬ ወይም ጠይቄ አይደለምና በመተርጎሙ እንኳን ባይሆን ባተረጓጎሙ ቢኖር ቅሬታ፤ አስቀድሜ ይቅርታ እጠይቃለሁ።*

***********************************************************



ህይወታቸውን ያጡ ወታደሮች ብዙዎች ነበሩ። አንደኛው ግን ከሌሎቹ ይለያል። በድን አካሉ በሠንደቅ ዓላማ የተጠቀለለ ሲሆን አብሮም ሕይወቱን ያጠፋበት ማስታወሻ ይገኛል። የተቀሩት ወታደሮች ግና የበረሃው ቃጠሎና እምቅ ዓየር በፈጠሩት ውህደት፤ በድካምና በሰውነት አለቅጥ መቀዝቀዝ እምሽክ ብለዋል። በቀይ ባህር ዳርቻ በሚገኙት በምፅዋና በአሰብ መካከል በዓለም እጅግ አስከፊው የተፈጥሮ ከባቢ ይገኛል። የእኔ ብርጌድ የተላከው በዚህ ክልል አቅጣጫውን ስቶ የጠፋውን የሻምበል ጦር ለመታደግ ነበር። ከፊት ለፊቴ የሚገኘው ህይወቱ ያለፈው ወታደር የሻምበልነት ማዕረግ አለው። እሱ በአዝጋሚ ሞት ጣዕሩን ከማብዛት ራሱን አጥፍቷል። ሰውነቱ ከተገነዘበት ሠንደቅ ዓላማ ጠርዝ የተቋጠረው ማስታወሻ እንዲህ ይላል፤ ***"ሠንደቅ ዓላማችን ሆይ፤ ሰላንቺ ተዋጋሁ፤ እነሆም ስላንቺ ምትኩ። ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር"*** ተንበረከኩ። በሻምበሉ ደም የዋጀውን ሠንደቅ ዓላማ በእጄ ያዝኩ። እና ሳምኩት። የታመቀ እንባ ከውስጤ ሊገነፍል ፈለገ። ማንባት ግን አልቻልኩም። በዚያ በረሃ የረገፉትን ሁሉንም አፈር አለበስናቸው። ቀበርናቸው። ሻምበሉንም የኢትዮጵያን ሠንደቅ ዓላማ እንደለበሰ ቀበርነው። (ሙሉ ታሪኩን "ክህደት በደም መሬት" በሚለው መፅሀፌ ያገኟል)።



የራሴን የጦር አካዳሚ የትምህርት ጓደኞቼን ጨምሮ በሺህ የሚቆጠሩ ወታደሮችና ባለማዕረጎች በጠላት እጅ ከመማረክ ይልቅ በሠንደቅ ዓላማቸው ራሳቸውን ጠቅልለው በገዛ እጃቸው ህይወታቸውን የነጠቁ ናቸው። ሜጀር ጄኔራል አምሃ ደስታ፤ *ሥመ* ጥር የአየር ሃይል ኮማንደር፤ ራሱን የሰዋው *__በዚህች ሠንደቅ ዓላማ__* ሰውነቱን ጠቅልሎ ነው።



በዚህ ምድር ላይ ከሚገኙት ባንዲራዎች ሁሉ ጥልቅ ፍቅርን እና ኩራትን ፈንቅሎ የሚያወጣ እንደ እርሷ ያለ የለም። በምፅዐት ፊት ተስፋንና ጀግንነትን የምታጎናፅፍ ባንዲራ እንደርሷ ከቶም የለም። እንደርሷም ያለ ቅዱስና ክቡር ባንዲራ የለምና። በድፍን አፍሪካ እንደርሷ ዘመናትን የተሻገረ አንጋፋ ባንዲራ የለም። *__ይህቿ ሠንደቅ ዓላማ__* ይላሉ ብላቴን ጌታ ህሩይ፤ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ982 እና በ958 መካከል በቀዳማዊ ምኒልክ የተቀረፀች ናት። እናም በብሄራዊ ሠንደቅ ዓላማነቷ በዓለም አዛውንቷ ሆና ትገኛለች። *__ይህቿ ሠንደቅ ዓላማ__* ድልን በተጎናፀፍንበትም ሆነ ሽንፈትን በቀመስንበት

ጦርነቶች ሁሉ ላይ ተገኝታለች። ***ይህቺ ሠንደቅ ዓላማ*** ከባርነትና ከቅኝ ገዢዎች ነፃ የመውጫ ተምሳሌ ሆና የአፍሪካውያን እና የራስ ተፈሪያን ባንዲራ ሆናለች።



***ይህቺ ሠንደቅ ዓላማ*** የነፃነት፤ የተስፋ፤ የአንድነት፤ የሉዐላዊነትና የክብር ምልክት ሆናለች። በምድረ ኢትዮጵያ ለሚገኙ ጎሳዎች፤ እምነቶች ወይም ሀይማኖቶች ሁሉ የመተሳሰር ወይም የአንድነት ምልክት ወይም ተምሳሌ ናት። ሠንደቅ ዓላማችን ከፍ ስትል ተስፋችንም አብሮ ከፍ ይላል። ከጠላት ጋር ስትገጥም፤ ስትዋጋ፤ ስሜትህን ፈንቅሎ የሚያንደረድርህ ሃይል ሠንደቅ ዓላማ ነው። የሠንደቅ ዓላማህን መዝሙር ስትዘምር ሠማዕታቱን ሁሉ እየዘከርክም ነው። ከሌሎቹ ጋር በህብረት ሆነህ ስትራመድ የህዝባችንን የማይቀለበስ የአንድነት መንፈስ ትጎናፀፋለህ። የሠንደቅ ዓላማህን ውብ ህብረ ቀለማት ስትመለከት ከውስጥህ ተስፋ ይፈነጥቃል፤ የአብናቶችህንም ታላቅ ገድለ ታሪክ ያስታውስሃል። ሠንደቅ ዓላማህን ስትይዝና ከፍ ስታደርግ አብሮም በውስጥህ አክብሮታዊ ፍርሃትና ክቡድ ሃላፊነት ይሰርፃል።

***ይህቺ ሠንደቅ ዓላማ*** ዘለዓለማዊ ህይወት አላት። የወኔ፤ የሠላም፤ የጀግንነትና የአንድነትን መንፈስ የምትረጭ ናትና - ሁሌም ትመለካለች። ጓደኛዬ ሻምበል ሳህሌ ባንዲራ በመስቀል ሂደት ላይ የነበረ ወታደር በስህተት አምልጦት ባንዲራው ሲወድቅበት ቢመለከት እጅግ ተቆጣ። ወታደሩም ከማፈሩ ብዛት ይቅርታ ጠይቆ ሻምበል ሳህሌ ቅጣት እንዲበይንበትም ጠየቀው። ከሁዋላው ተሰልፈው የነበሩትን ባልደረቦቹንም ይቅርታ ጠየቃቸው። ባንዲራው በመውደቁ የባንዲራውን ክብር የጣለ ያህል ተሰማው። ለበርካታ ቀናትም መንፈሱ ተረበሸ። ምክንያቱም እያንዳንዱ ወታደርና ባለማዕረግ የታነፀበት ባህል ከማንኛችንም በላይ ባንዲራ ዋጋ ያለው በመሆኑ ባንዲራ ተሸክመን ብንወድቅ እንኳ መጀመሪያ መሬት መውደቅ የሚገባው ሰውነታችን እንጂ ባንዲራ አለመሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅብናልና።

"በባንዲራ !!! እንዳትንቀሳቀስ !!!" አንድ ክፉ ሁኔታ በተፈጠረበት ቦታ የሚገኝ የድርጊቱ ፈፃሚ ከአድራጊቱ ሸሽቶ ለማምለጥ ቢሞክር "በባንዲራ !!! ወድቃ በተነሳችው ፤ እንዳትንቀሳቀስ !!!" ከተባለ ባለበት "ገጭ" ብሎ ከመቆም ሌላ ሮጦ ለማምለጥ መሞከሩ የማይታሰብ ነው። ተሰብሳቢውም የባንዲራን ጥሪ ሲሰማ ባለበት ረግቶ በመቆም ሂደቱን ይከታተላል። እነሆ ባንዲራችን ይህን ያህል ክብር የተጎናፀፈች ነበረች።

***ይህቺ ባንዲራ*** ፤ አረንጓዴ ቢጫና ቀይ፤ ሳትደበዝዝ ሳትቀየር ህዝባችንን ለዘመናት ይዛ እዚህ ደርሳለች።




ይህቺ ባንዲራ ስትዋረድ፤ ስሟ ሲጠፋ፤ ያለ መልኳ መልክ ሲወጣላትና ስትንጓጠጥ - እነሆ ይህን ጊዜ አንድነታችን ባይፈርስም እንኳ መንገጫገጭ ይጀምራል።

ይህቺን ሠንደቅ ዓላማ ስታከብር፤ የምታከብረው ለምዕተ ዓመታት የቆመችለትን ዓላማና ስለዚህችም ታላቅ አገር ሲሉ መሥዋዕትነትን የከፈሉትን ሁሉ ማክበርህም ጭምር ነው። የዚህች ሠንደቅ ዓላማን ተምሳሌትነት፤ ቅርፅና መልክ በማንኛውም መልኩ ስትቀይር ቅድስናዋን ማርከስና ሀጢያትም መፈፀም ይሆናል። ህወሃት ይህቺን ባንዲራ በአህያ ጀርባ ላይ ጭኖ አደባባይ የወጣ ጊዜ ዘመን የማያጠግገው /የማይሽረው/ ቁጭትና ንዴት ፈጥሯል። ይህ ርኩሰት ባንዲራዋ ለቆመችለት ዓላማ የተሰዉትን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሠማዕታትን የዘለፈ ነበር።

ኤርትራ ከኢትዮጵያ እስከተገነጠለችበት ወቅት ድረስ በኤርትራ ደጋማው ክልል የቀብር ሥርዐት ይካሄድ የነበረው በዚህች ሠንደቅ ዓላማ ተሞሽሮ ነበር። በክብረ በዓላት ወቅትም በእያንዳዱ ቤት ባንዲራ ይሰቀል ነበር። በምድረ ኤርትራ የኢትዮጵያ ሠንደቅ ዓላማ ይከበር የነበረበት ሁኔታ ከሌሎች {ከፍላተ ሀገራት} ሁሉ

የተለየ ነበር። ታዲያ አስገራሚው የታሪክ ምፀት፤ በበርካታ ትውልዶች ይከበር ከነበረው ሠንደቅ ዓላማ፤ “የሀገር ፍቅር ማህበር” በተሰለፈባቸው አደባባዮች ሁሉ ከእናት ሀገር ኢትዮጵያ ጋር የመዋኻድ ጥያቄውን ሠንደቅ ዓላማውን ከፍ አድርጎ በማውለብለብ ይጠይቅበት ከነበረበት - ኤርትራ ራሷን ከራሷ ሀገር የመገንጠሏ ታሪክ ነው። ከወራሪዎች ጋር የተዋጋናቸው በርካታ ጦርነቶች የተካሄዱት በሰሜን - በትግራይና በኤርትራ ነው። ወራሪዎች ከቀይ ባህር እየዘለቁ በመጡ ቁጥር በተካሄዱት ጦርነቶች ይህ ሠንደቅ ዓላማ ከሌሎች ይበልጥ በኒህ ግዛቶች ይከበር ነበር።

ሌላው አስገራሚ ምፀት ደግሞ - ይህቺን ሠንደቅ ዓላማ ይዘው አእላፍ የተሰዉላት ትግራይ - ባንዲራን ያዋረደች መሆንዋ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ (መለስ ዜናዊ) ይህ ባንዲራ ቁራጭ ጨርቅ ነው - ነበር ያለው?



ጤናማ አእምሮ አለኝ ከሚል ኢትዮጵያዊ እንዲህ ያለ {ነውረኛ} ቃል ይወጣል ብሎ ማመን ከቶም ይከብዳል። እንዲህ ያለው የክህደትና የውርደት ተግባር ይቅርታ የማያስገኝ ብቻ ሳይሆን በእኛ ዘመን ቢሆን ኖሮ የሞት ብይን የሚያሰጥ እንጂ።

እነሆ ዛሬ ግን ዕድሜ በአንድነታቸው ፀንተው በየአቅጣጫው መሥዋዕትነትን በመክፈል ላይ ላሉት ኢትዮጵያውያን ይሁንና ይህቺ ሠንደቅ ዓላማ ከፍ ብላ እየተውለበለበች ነው። የጨለማው ዘመን እየተገፈፈና ጥሩ ቀን እየቀረበ የመምጣቱ ምልክት ይህ ነውና። ሠንደቅ ዓላማችን በኢትዮጵያ ምድር ሁሉ ከፍ ብላ መውለብለብ ስትጀምር - ያኔ የኢትዮጵያ ትንሣኤ ሆነ ማለት ነው። ***ይህንን ባንዲራ* መፈለግ አንድነታችንን መፈለግ ነውና።**

-------------------------------------- / / / ------------------------------------------

**ምንጭ፤** Claiming This Flag! (Dawit Wolde Giorgis)

**ፎቶ፤** በጎንደርና በጎጃም ከሐምሌ 2008 ዓ/ም ጀምሮ በመካሄድ ላይ ካለው ህዝባዊ ትግል የተገኘ።

ሲድኒ አውስትራሊያ፤ ጳጉሜ 2008 ዓ/ም (ሴፕቴምበር 2016) ተተረጎመ። mmtessema@gmail.com